Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**ይፋዊ መግለጫ**

**ጥር 27 2017**

ይህ ይፋዊ መግለጫ በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ ወይም በኢትዮጵያ የንግድ ህግ መሰረት ከህዝብ ገንዘብን በመሰብሰብ የተቋቋሙ ኩባንያዎችን ይመለከታል። በተለይም **በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ እና ኢንዱስትሪ ሳይገደብ** ከአምሳ (50) በላይ የአክስዮን ባለቤቶች ያሏቸው ኩባንያዎችን ይመለከታል።

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ግብይት መመሪያ ቁጥር 1030/2024 (“መመሪያ”) ከህዳር 5, 2017 ጀምሮ ስራ ላይ መዋሉ ይታወሳል።የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን (“ባለስልጣን”) ለኢንቨስተር ከለላ የመስጠት እንዲሁም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የማውጣት እና የግብይት ስራ ስርዓትን የተከተለ፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽነት በሰፈነበት ሁኔታ የሚካሄድበትን የተሟላ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳርን ለመፍጠር የተነሳበትንአላማ ከግብ ለማድረስየሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለህዝብ የማቅረብ እና ሽያጭን የሚቆጣጠር የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል።

**የይፋዊ መግለጫው አላማ**

መመሪያው ከሚያስተዋውቀው አዲስ የቁጥጥር ስርዓት ጋር ተያይዞ ይህ ይፋዊ መግለጫ ለቁጥጥር ሂደቱ የሚረዱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ያለመ ነው። በዚህም መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች ነባር አክስዮኖቻቸውን ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለማምጣት ስለአክስዮኖቹ አስፈላጊውን መረጃ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን። በዚህ መልኩ የሚሰበሰበው መረጃም በገበያው ውስጥ ጠንካራ መረጃ ይፋ የሚደረግበት እና ግልጽነት የተሞላበት የገበያ አሰራር እንዲፈጠርያግዛል።

ስለሆነም በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች ይህ ይፋዊ መግለጫ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ እስከ መጋቢት 1, 2017 ዓ.ም. ጊዜ ውስጥ የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለስልጣኑ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን።

1. በሙሉ የተከፈሉ እና ቃል የተገባባቸው አስክስዮኖችን ጨምሮ ጠቅላላ የአክስዮን ብዛት፣
2. የባለአክስዮኖቹን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም በባለአክስዮኑ የተያዘው የአክስዮን ብዛትን የሚያካትት የባለአክስዮኖች ዝርዝር፣
3. አክስዮኖቹ ከወጡበት ቀን አንስቶ ያለው የነባር አክስዮኖች ዋጋ፣
4. የሁሉም ነባር አክስዮኖች የወጡበት ወይም ለሽያጭ የቀረቡበት የሽያጭ ጊዜ መጀመሪያ እና መጠናቀቂያ፣
5. የአክስዮን ሽያጭ ጥሪውን ለማቅረብ ጥቅም ላይ የዋለ የሽያጭ ማቅረብያ ሰነድ ኮፒ፣
6. ሽያጩን አስመልክቶ የቀረበ ማስታወቅያ ይዘትና የቀረበበት የሚዲያ አማራጭ እንዲሁም
7. ለነባርም ሆነ አዲስ ባለአክስዮኖች የቀረበ ማንኛውም ያልተጠናቀቀ ለህዝብ የቀረበ የአክስዮኖች ሽያጭ አክስዮኖቹ እንዲውጡ የተፈቀደበት የባለአክስዮኖች ቃለ-ጉባኤን እንዲሁም ሌሎች ከአክስዮኑ መውጣት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችን አካተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Minaye Corporate Building 15th Floor,
Flamingo Area, Kirkos Addis Ababa, Ethiopia
+251 115578250 | +251 115578310
communication@ecma.gov.et
ecma.gov.et

**የመረጃ አቀራረብ**

የመረጃ አቅራቢ ኩባንያው አስተዳደሮች የሚቀርቡትን ሰንዶች የያዘ መግለጫ ላይ በመፈረም የቀረቡት ሰነዶችና መረጃዎች ትክክለኛ እና የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ማመልከቻዎቹ፡-

- በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ በሚገኘው የባለስልጣኑ ዋና መስርያ ቤት ምናዬ ህንጻ 17ተኛ ፎቅ በወረቀት መቅረብ አለበት።
- የሰነዶቹ ቅጂ በ lgizachew@ecma.gov.et እንዲሁም smohammed@ecma.gov.et የኢሜል አድራሻ መላክ አለባቸው።

**አስፈላጊ መረጃ**

በተቀመጠው የጊዜ ገድብ ውስጥ ከላይ የተጠየቁትን መረጃዎች የማያቀርቡ ኩባንያዎች ማንኛውም አይነት የአክስዮን አቅርቦታቸው ከህዳር 5, 2017 ዓ.ም በኋላ እንደቀረበ ተደርጎ ይወሰዳል።

**ማሳሰብያ**

**ነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፡** በዚህ ይፋዊ መግለጫ መሰረት የሚቀርብ መረጃ የነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባልስልጣኑ እንደማስመዝገብ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። በህዝብ የተያዙ ኩባንያዎች የመመሪያውን የምዝገባ መስፈርቶች በማሟላት ከህዳር 5, 2017 ዓ.ም አንስቶ በሚቆጠረው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል።

**ያልተጠናቀቁ ሽያጮች፡** በተጨማሪም መመሪያው ስራ ላይ ከዋለበት ቀን አስቀድመው ሽያጫቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከህዳር 5 አንስቶ በሚቆጠረው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መመዝገብ እንደሚገባቸው ይደነግጋል።

**አዲስ ሽያጭ፡** እባኮትን ማንኛውም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለሽያጭ ከመቅረቡ አስቀድሞ መመዝገብ እንዳለበት ልብ ይበሉ። በዚህም መሰረት አዲስ ሽያጭ ማካሄድ የሚፈልጉ ኩባንያዎች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን አስቀድመው በባለስልጣኑ ያስመዝግቡ።

እነዚህን የምዝገባ መስፈርቶች አለማሟላት በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት ቅጣትን ያስከትላል።

ስለዚህም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኩባንያዎች በሙሉ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ወደ የሚደረግበት የካፒታል ገበያ የሚደረገውን ሽግግር ያግዝ ዘንድ እነዚህን መስፈርቶች እንዲያከብሩ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን

ጥር 27 2017